# “ሁለገብ” አዲሱ የትግል ገድል

## ከምስማኩ ተሊላ ፡ ለንደን 25/05/2009

ቀደም ሲል የነበሩት የመሳሪያ ትግል ጅምሮች በሙሉ ቀስ በቀስ ከስመዋል። ወያኔ መድረሻ ያሳጣቸው ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ደግሞ የትጥቅ ትግል ለመጀመር በጎረቤት አገር ድጋፍ ወደ አገር እንሸጋገራለን በሚል ተስፋ በአካባቢ መንግስታት በተለይ በተለይ ደግሞ በሻቢያ እጅ ወድቀው የወያኔ ማስፈራሪያ በመሆን ተወስነዋል።

ከዚህ ሁሉ በተለዩ መልኩ ደግሞ በጎበዝ አለቃ ተሰባስበው፤ መሳሪያ አንስተው እንቢ ለወገኔ እንቢ ለአገሬ ብለው በበረሃ የሚንቀሳቀሱ ወገኖች እንዳሉ ከቅርብ አዋቂዎች ይሰማል። እነኝህ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ዱር ቤቴ ብለው ሲያገኙ እየበሉ ሲአጡ ጦም እያደሩ መንቀሳቀሳቸውን ቀጥለዋል። የወደፊቱ ቁርጠኛ ትግል እርሾ እነኝህ ደኑ ቤቴ ብለው በአገር የሚንቀሳቀሱ ጀግኖች ናቸው።

ከዚህ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ደግሞ በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን ብለው በወያኔ አይነቁራኛ እየተጠበቁ የሚንቀሳቀሱ ወደ መቶ የሚደርሱ ድርጅቶች እንዳሉ የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ይወሽክታል። ከዚህ ሰላማዊ ሰልፈኛ መሃል በአብዛኛው የወያኔ/ኢህአደግ ተለጣፊ ነው። ከፊሉ ደግሞ አንቀጽ 39ን ተንተርሶ ከቀናው ወደ ምኒልክ ግቢ ለመግባት ይህ ካልሆነ ደግሞ ክልሉን አጠናክሮ በርቀት ራእይ ሌላ ድኩማን ሪፑብሊክ አቁሞ እንደ ሻብያ ባንዲራ እያውለበለበ ህዝቡን ረግጠ ለመግዛት የሚአለም ነው።

አንፃራዊ በሆነ መልኩ ለኢትዮጵያዊነት ሙብት መረጋገጥ የሚታገሉትን ወገኖች አሉ። እነዚህ ወገኖች ግን ብዙና የከፋ ችግር አለባቸው። በአንድ ግንባር ወያኔ፣ ስንጎ ይዞ በየምክንያቱ እንዳይንቀሳቀሱ ያግዳቸዋል። የ97ቱ ህዝባዊ ድል እንዳየደም የተቀነባበረ አፋኝ እርምጃ እየወሰደባቸው ነው። በሌላ ግንባር ጠባብ ብሄርተኞች፣ በሚአወሩትና በሚአስወሩት እንቅስቃሴአቸው እንዳያድግ ያደርጋሉ። በሶስተኛ ግንባር የኢትዮጵያን ደህንነት የማይፈልጉ ሃይሎች በሩቅ በታሰበ ስልት እያደናቀፉ፣ ለደሞክራሲ፣ ለእኩልነትና፣ ለአነደነት፣ የሚደረገው ትግል በእንፉቅ እንዲሄድ እያደረጉት ነው።

ይህ ሁሉ ምስቅልቅል ባለበት ሁኔታ ደግሞ ዛሬ ሌላ ውል የለሽ የትግል ስልት ይዘው ብቅ ያሉ ክፍሎች አሉ። ይህን ውል የለሽ የምንለው አካሄድ ‘ሁለገብ’ ትግል ይሉታል። ይህን የሚሉ ሰብስቦች በቅርቡ ወደ ሁለት ቢደርሱም ‘ሁለገብ’ ትግልን በዋናነት የሚአራግበው ድርጅት በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የሚመራው ግንቦት7 የሚባለው የዲአስፖራ እንቅስቃሴ ነው።

'ሁለገብ' ትግል ምን ማለት ነው? ግንቦት 7 በድርጅት ፕሮግራሙ እንዲህ ይላል፡ "ትግላችን ቀኖናዊ በሆነ መንገድ የሚከተለው የትግል ስልት የለውም። የሃገራችንን ተጨባጭና የተለየ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ማንኛውንም አይነት ሁለገብ የሆነ ትግል በተግባር ይውላል።"

ይህ ድርጅት የሚጠቀምበት 'ቀኖናዊ ያልሆነ' ማለትም ተለይቶ የተያዘ ስልት የሌለውና ማንኛውንም አይነት ወይንም 'ሁለገብ' የሆነ ትግል እጠቀማለሁ ሲል ብዙ ሕጋዊና ሕገወጥ ሁኔታዎችን እያለዋወጠ ለመጠቀም ማሰቡ አካሔዱን በጣም አደገኛ ያደርገዋል። 'ሁለገብ' ሲል በዚህ አጭር አሰተያየት ለመግለጽ የሚከብዱ ሁኔታዎችን ሁሉ ያጠቃልላል። አቅም ካለ የፊት ለፊት ውጊያ መግጠም በሁለገብ ይመደባል። የሽምቅ ውግያም እንደዚሁ ነው። አሸባሪ እርምጃም ሁለገብ ሊሆን ይችላል፡ ሌላም ሌላም። እንደዚህ በክፍተት የተያዘና ከላይ በሚታዘዝ የትግል አካሄድ ብቻ የሚመራ ድርጅትን ማን አምኖ ይከተላል? ትግሉ ከዛሬ ነገ ምን ይዞት እንደሚኖረው ካልታወቀ ሰው ምኑንና የቱን አይቶ ይደግፋል? በአንፃሩ ደግሞ በየስብሰባው የሚገኘው ሰው በአፍ ከመደገፍ አልፎ 'ለሁለገብ ትግል' የገንዘብ የሞራል የተሳትፎ አስተዋጽዎ ሲአደርግ ይታያል። እዚህ ላይ መቅረብ ያለበት ጥያቄ አለ። ይህ ተባባሪ የሆነው ዳያስፖራ የድርጊቱ ሂደትና ውጤት ምን እንደሚሆን ግምት አልው ወይስ በደፈናው እንደሆነ አድርገው ችግራችን ይፍቱልን በሚል ተስፋና ምኞት ነው ይህን አካሄድ የሚደግፈው።

አንዳንዶች የግንቦት 7 ሰዎች የደቡብ አፍሪካንና የአየርላንድን የትግል ታሪኮች በማጣከስ ያንኑ በኢትዮጵያ መተግበር ይቻላል ይላሉ። ይህን ማለት ደግሞ ግንቦት7 ሕጋዊና ሕጋዊ ያልሆነኑ አካሎች ኖረውት ሁለቱን ደግሞ በህቡእ የሚአገናኝ አካል ወጣ ገባ እያለ የወያኔ ሴኩሪትና ካድሬ ሳይነቃበት ሁለገብ ትግሉን ያንቀሳቅሳል ማለት ነው። ይህ ምኞታዊነት እንጂ በተግባር ሊውል የሚችል የትግል እቅድ አይደለም።

የግንቦት7ን ሁለገብ ትግል ለአመት ያህል አዳምጠን እስካሁን በተጨባጭ የታየ ነገር የለም። በቅርቡ ግንቦት7 ውጤት እያሳየ ነው በማለት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አውሮፓን እየዞረ ነው። 'መልካም ዜና' በማብስር ላይ ነው ይባላል። በእንግሊዝ አገር የሚኖረውም ዳያስፖራ ተራውን ጠብቆ በስብሰባ እንዲገኝ በቤተክርስቲአን ሳይቀር በበራሪ ወረቀት እየተጠራ ነው። በዚህ ስብሰባ ለመገኘት ከፍ ያለ ገንዘብ እንደሚከፈል ይነገራል። የእንግሊዝ ዳያስፖራ ለቅንጅት ድጋፍ ያዋጣው ከሰላሳ ሺህ ፓውንድ በላይ የት እንደ ደረሰ ሳይገለጥለት አሁን እንደገና ለ3ኛና 4ኛ ዙር ሌላ ገንዘብ እንዲሰጥ እየተጠየቀ ነው። የቅንጅት ወራሾች ነን የሚሉት እነብርሃኑ ነጋ የቅንጅትን ገንዘቡን እንጂ ራእዩንና ሃላፊነቱን አይፈልጉትም። ይህ ቢሆንማ የሰንት ዜጋ ህይዎት ያለቀበትን ድርጅት ዘግተው ወደ ውጭ አገር አይፈረጥጡም ነበር። ውጭ ከወጡ በሑአላ ደግሞ ቅንጅት ለምን እንደፈረሰ ለዳያስፖራው ሳያስረዱ እንደ አዲስ ተመልሰው "ሁለገብ ትግል" እያሉ ያተራምሱታል። በእንደዚህ አይነቱ የክደትና የሸፍጥ አካሄድ ትግሉ ፍሬ ያለው

ውጤት አይኖረውም። በዚህ አካሄድ ኢትዮጵያ በዎያኔ መዳፍ እንደተጨፈለቀች መቀጠሏ ነው። ዲያስፖራው ለኢትዮጵያ ትንሳኤ የራእይ አስትዋጽኦ ለማድረግ አቅም ቢአንሰውም ደክሞ ያገኘውን ገንዘብ ለመጣ ለሄደው በመወርወር የኢትዮጵያን ሕዝብ አባዜ ባያራዝመው መልካም ነው።

በአንድአንድ የፖለቲካ ተመልካቾቸ አስተያዬት ‘ሁለገብ’ ውጤት የለሽ መሰዋእትነት የሚአስከትል የትግል እንቶ ፈንቶ እንጅ ኢትዮጵይውያን ካሉበት ጨለማና አደገኛ በዘር ላይ ከተመሠረተ ፖለቲካ ነጻ እንደማያወጣ ዲያስፖራው እንዲያውቀው ያሰፈልጋል። በሌላ መልኩ ደግሞ እንዲህ ያለ አቅጣጫው ያልታወቀ ትግል ብዙ እንደሚአዘናጋ፡ በተለዋዋጭነቱ ደግሞ የተሻለ አማራጭ መስሎአቸው የተከተሉትንና የደገፉትን ሁሉ ያላሰቡት ገደል እንደሚጨምራቸው ማወቅ አለባቸው። አሁን ሌሎችም ‘ሁለገብ’ የሚሉ ድርጅቶች ብቅ ብቅ እያሉ ስለሆነ ግንቦት7 የፈጠረው ውዥንብር እየተስፋፋ መሄዱን የሚአሳይ ምልክት ነው። ለእንደዚህ ዐይነቱ ዉል የለሽ የትግል አካሄድ ድያስፖራው አባሪ ተባባሪ ባይሆን፡ የሞራልና የማቴሪይል ድጋፉን ወይ በቁርጥ መሳሪይ አንስተው ለሚንቀሳቀሱት ጀግኖች፡ ወይ ደግሞ በአገር ውስጥ ከተለጣፊዎችና የዘር ፖለቲካ አራጋቢዎች ንክኪ ሳይኖራቸው ለኢትዮያ ህዝብ መብት መከበር፡ ለእኩልነትና ለአንድነት ለቆሙ ድርጅቶች ቢያውለው የሰደት ሕይዎቱ አጭር ሊሆንለት እንደሚችልና የወገኑ ሰቆቃ ዘላቂ መፍትሄ ሊያገኝ እንደሚችል ሊረዳ ይገባል። በስተቀር ዉሃን ቢወቅጡት እንቦጭ ብቻ ሳይሆን ዉሃዉም ፈሶ ያልቃል። ኢትዮጵያም እንዳልነበረች የመሆን እዉነታ ባጭር ጊዜ ሊከሰት ይችላል።